# ባለሥልጣኑ የትብብር ስምምነት ተፈራረመ

*በዘላለም ምህረቱ*

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከአለም የጉምሩኮች ድርጅትና ከእስራኤል የጉምሩክ እና የታክስ ባለሥልጣን ጋር የሶስትዮሽ የትብብር ስምምነት ተፈራረመ፡፡ ስነ-ሥርዓቱ የተካሄደው ሰኔ 2/2002 ዓ.ም. በቤልጄየም ብራስልስ በአለም የጉምሩኮች ድርጅት ዓመታዊ ጉባኤ ላይ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስምምነቱን በኢትዮጵያ በኩል የፈረሙት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መላኩ ፈንታ ሲሆኑ በእስራኤል መንግሥት በኩል የአገሪቱ የታክስ ባለሥልጣን የጉምሩክ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሚስተር ዶርን አርቤሊ እንዲሁም በአለም የጉምሩኮች ድርጅት በኩል ዋና ፀሐፊው ሚስተር ኩንዮ ሚኩሪያ ናቸው፡



ከግራ ወደ ቀኝ ሚስተር አርቤሊ፣ ሚስተር ሚኩሪያ እና አቶ መላኩ ፈንታ ስምምነቱን በተፈራረሙበት ወቅት

ስምምነቱ ፊርማ በኂላ አቶ መላኩ ፈንታ እንደገለፁት የትብብር ስምምነቱ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስትራቴጂካዊ ግቦች መሣካትና አገራችን ለተያያዘችው ቀጣይነት ያለው የዕድገት ግስጋሴ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

የትብብር ስምምነቱ ዘመናዊና ውጤታማ የሆነ የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓት ለማስፈን ከፍተኛ የሆነ የማስፈፀም አቅምን የሚያጐለብት መሆኑን የአለም የጉምሩኮች ድርጅት ፀሐፊ ገልፀዋል፡፡ ሚስተር አርቤሊ ደግሞ ስምምነቱ በኢትዮ እስራኤል የሁለትዮሽ ግንኙነት ላይ የበለጠ መጠናከርን እንደሚፈጥር ጠቁመዋል፡፡